የመቐለ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት ለ2011 ዓ/ም በጀት ዓመት የሚያገለግል ኤች ዲ ፒ ትቦ (HDPE PIPES፣ ዲ ሲ ኣይ (ሲኣይ)፣ ጂኤስ (ጂኣይ) ትቦ እና መገጣጠሚያዎች (DCI/CI GS/SI PIPES & FITTINGS) እና የኤች ዲ ፒ መገጣጠሚያዎች (HDPE FITTINGS) ግዢ አወዳድሮ በግልጽ ጨረታ ለመግዛት ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ሓሙስ ጉንበት 8, 2011 (ከ 7 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: ጉንበት 23, 2011 4:00 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:130000
- ቦታ:መቐለ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:200
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ጉንበት 23, 2011 4:30 ጥዋት
- ምድብ: ቱቦታትን ኣክሰሰሪታትን/ ቅፋሮ ማይ ኢንጂነሪንግ ማሺነሪ, ኣቁሑትን ኣክሰሰሪ/

- ሎት አንድ ፡- ኤች ዲ ፒ ትቦ (HDPE PIPES
- ሎት ሁለት ፡- ዲ ሲ ኣይ (ሲኣይ)፣ጂኤስ (ጂኣይ) ትቦ እና መገጣጠሚያዎች (DCI/CI GS/SI PIPES & FITTINGS) እና የኤች ዲ ፒ መገጣጠሚያዎች (HDPE FITTINGS) ግዢ አወዳድሮ በግልጽ ጨረታ ለመግዛት ስለፈለገ በጨረታው መሳተፍ ለምትፈልጉ ተጫራቾች ጥሪውን ያቀርባል።

1. የታደሰ ህጋዊ ንግድ ፍቃድና የአቅራቢዎች መታወቂያ ፍቃድ ያላቸው።

2. ቫት የተመዘገበና የመጨረሻ ወር ቫት ዲክለር ያደረገ ቲን ቁጥር ማቅረብ የሚችል።

3. የጨረታው ዶክሜንት የማይመለስ ለእያንዳንዱ ሎት ብር 200/ሁለት መቶ ብር / በመክፈል መቐለ ውሃ አገልግሎት ጽ/ቤት በመምጣት የጨረታው ዶክሜንት ከደጋፊ ሥራ ሂደት ግዥ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ቢሮ ቁጥር 13 መግዛት ይችላሉ።

4. የጨረታ ዶክመንቱን ማስገባት የሚቻለው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 15ኛው ቀን የ2011 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ወደ ጨረታ ሳጥን ማስገባት ይችላሉ።

5. ጨረታው የሚዘጋው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15ኛው ቀን 2011 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በእለቱ 4፡30 ሰዓት ተጫራቾች ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል።

6. ሁሉም ተጫራቾች ለሎት አንድ 130,000፣ ለሎት ሁለት 130,000 የጨረታ ማስከበሪያ በCPO በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በማይሻር ሌተር ኦፍ ክሬዲት የቀረበ ዋስትና ጥሬ ገንዘብ የተረጋገጠ ቼክ ወይም የክፍያ ትእዛዝ በማስያዝ ይጠበቅባቸዋል።

7. ተጫራቾቹ ነጠላ ዋጋና የጠቅላላ ዋጋ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት። በተጨማሪም በጨረታ ዶክመንቱ ውስጥ የተዘጋጁ ፎርማት ተሞልተውና ተፈርመው መቅረብ አለባቸው።

8. በዶክመንቱ ከተሰጠው ስፔስፊኬሽን ውጪ የሚቀርብ ተቀባይነት የለውም።

9. የጨረታው አሸናፊ ውል ማስከበሪያ ካሸነፈው ዋጋ በCPO በተረጋገጠ የባንክ ጋራንቲ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና የውል ማስከበሪያ (Performance bond guarantee) 10% ማስያዝ የሚችልና በ3 ቀን ውስጥ ውል አስሮ በዶክመንቱ በተጠቀሰው ቀን ንብረቱን ማስገባት የሚችል።

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle

10. በጨረታው ሂደት ጨረታውን ለማዛባት ለማጭበርበር የሞከረ ተጫራች ከጨረታው ውጭ እንደሚሆንና በመንግሥት ግዢ እንዳይሳተፍ ለማድረግ ወደ ክልሉ ፋይናንስና ፕላን ቢሮ ደብዳቤ እንደምንጽፍ

11. የጨረታ ሳጥኑ ከተዘጋ በኋላ የሚመጣውን የጨረታ ዶክመንት ተቀባይነት የለውም።

12. ጨረታው ፀንቶ የሚቆየው ጨረታው ከተከፈተ ለ60 ተከታታይ ቀናት ብቻ ነው::

13. ጽ/ቤቱ ጨረታው እንደ አስፈላጊነቱ ከያንዳንዱ ነጠላ ዋጋ በ20% የመጨመር ወይም የመቀነስ መብቱ የተጠበቀ ነው።

14. የሚቀርበው ጨረታ ዶክመንት

14.1. ቴክኒካል አንድ ኦርጅናልና ሁለት ኮፒ ሰነድ ለየብቻው አሸጎ ማቅረብ የሚችል እንዲሁም

14.2. ፋይናንሻል አንድ ኦርጅናል ሁለት ኮፒ ሰነድ ለየብቻው አሸጎ ማቅረብ የሚችል መወዳደር ይችላል።

15. ጽ/ቤቱ ጨረታው በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

አድራሻ፡- ትግራይ መቐለ

ስልክ ቁጥር፡- 0344407335 / 0914755845

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle